# በሰቆጣ ቃልኪዳን ፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1039/2017 ላይ የተሰጠ አጭር ማብራሪያ

መንግስት ዕድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች በሆኑ ህጻናት ላይ የሚከሰተውን የመቀንጨር ችግር በኢትዮጵያ በ2022 ዓ.ም ዜሮ ለማድረግ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራምን በ2007 ዓ.ም ይፋ በማድረግ ትግበራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ የመቀንጨር ችግር ከፍተኛ የሶሺዮ-ኢኮኖሚና የልማት ችግር ነው፡፡ ምንም እንኳ ይህንን ችግር ከመቀነስ አንፃር አበረታች ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ሀገራችን ቃል ከገባቻቸው ካስቀመጠቻቸው ዓለም አቀፍና ሀገራዊ ግቦች አንፃር ሲታይ በብዙ መለኪያዎች ወደ ኋላ ቀርታለች፡፡

የኢትዮጵያ የጤናና ስነህዝብ ጥናት (EDHS) እና የኢትዮጵያ የምግብና ስርዓተ-ምግብ ጥናት (FNS) ዕድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናትን አስመልክቶ ባወጡት መረጃ መሰረት፣ እ.ኤ.አ በ2022 አጠቃላይ የመቀንጨር (Stunting)፣ የመክሳት (Wasting) እና ከክብደት በታች የመሆን (Underweight) ምጣኔው 39 በመቶ፣ 11 በመቶ እና 22 በመቶ በቅደም ተከተል ነው፡፡ ይህም ወደ ቁጥር ሲለዋጥ ተፅእኖውን በቀላሉ መረዳት ያስችላል፡፡ ለምሳሌ፣ የመቀንጨር ችግር ያጋጠማቸው ሕፃናት ቁጥር ብቻ ወደ 6 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፡፡

*Fig 1. Burden and trends in Ethiopia ( Source, EDHS, 2019 and EPHI FNS baseline survey, 2023)*




መቀንጨር የሶሺዮ ኢኮኖሚ ችግር ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ችግሩ በግለሰብ፣ በማህረሰብና ሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የአጭር እና የረዥም ተፅዕኖን የሚያስከትል ስር የሰደደ ችግር ሲሆን በህፃናት ጤና፣ የአዕምሮ ዕድገትና ሲያድጉ በሚኖራቸው የማምረት አቅም ላይ አሉታዊ ውጤት ያለውና የሀገሪቱን ዕድገትና ምርታማነትን የሚገታ ችግር ነው፡፡

በ2009 በተካሄደው የአፍሪካ ልማት ባንክ Cost of hunger ጥናት መሰረት ሀገራችን በየዓመቱ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ጥቅል ምርቷን 16.5 በመቶ ወይም በዓመት 55.5 ቢሊዮን ብር (USD 4.5 ቢሊዮን) ታጣለች፡፡ ይህም ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ከሚያጡት ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ ነው (ግብፅ 3.7 ቢሊዮን USD ፣ ኡጋንዳ 0.89 ቢሊዮን USD እና ሲዊዚላንድ 0.076 ቢሊዮን USD)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ 16 በመቶ የትምህርት የመድገም ምጣኔ መንስዔ በዚሁ በመቀንጨር ችግር የሚከሰት ሲሆን ከዚህና ከሌሎች የስርዓተ-ምግብ ችግሮች ጋር ተያይዞ በሚከሰት ሞት የተነሳ የሀገራችን አምራች ኃይል በዓመት ከ 1- 8 በመቶ እየቀነሰ ይገኛል፡፡

ችግሩ የከፋ እንደመሆኑ መጠን ይህንን ለመቅረፍ በስርዓተ-ምግበ ስራዎች ላይ የሚፈስ መዋለ ንዋይ ግኝት (Return) ከፍተኛ ሲሆን ይህም ምርታማነትን ይጨምራል፣ ከፍተኛ ገቢ ያስገኛል ዜጎች ጥራት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ የስችላል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት 1 ዶላር መዋዕለ-ንዋይ 138 ዶላርን ያስገኛል።

የኢትዮጵያ መንግስት የስርዓተ-ምግብ ችግርን ለመቅረፍ የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን ፕሮግራሞችን ቀርፆ በመተግበር ላይ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የብሄራዊ ስርዓተ-ምግብ ፕሮግራም I እና II (NNPI and II), የምግብና ስርዓተ-ምግብ ፖሊሲና ስትራቴጂ እና የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፍኖተ ካርታ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የሰቆጣ ቃልኪዳን የምግብና ስርዓተ-ምግበ ስትራቴጂ የትግበራ ማሳያ ሲሆን ዘርፈ ብዙ እና ድህነት ተኮር በሆኑ ስራዎች ላይ የሚያተኩር እና በአስራ አምስት የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲና ስትራቴጂ ፈጻሚ ሴክተሮች ቅንጅታዊ አሰራር ከፌደራል ጀምሮ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች የሚተገበር ነው። የሰቆጣ ቃል ኪዳን የ15 ዓመት ፍኖተ ካርታ ያለው ሲሆን በሶስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ በመተግበር ላይ ይገኛል።

መንግስት ከጆንሆፐኪንስ ዩኒቨርሲቲ እና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ባደረገው የተጽእኖ ግምገማ ጥናት ውጤት መሰረት የመጀመሪያው የሙከራ ትግበራ ምዕራፍ ለ5 ዓመታት ማለትም ከ2009 - 2013 ዓ.ም ድረስ በአማራ እና ትግራይ ክልሎች በ40 ወረዳዎች ሲተገበር ቆይቶ በዓመት እስከ 3 በመቶ አማካኝ የመቀንጨር ምጣኔ ቅነሳ በማስመዝገብና ወደ 110,000 የሚሆኑ ልጆችን ከመቀንጨርበመታደግ ፣1031 የጨቅላ ህፃናት ሞትን በማስቀረት ተስፋ ሰጪ ስኬቶችን በማስመዝገብ ተጠናቋል። ሁለተኛው የማስፋፋት ምዕራፍ (Expansion Phase) የሚባለው ሲሆን ይህም ከ2014 - 2018 ዓ.ም ድረስ በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ውስጥ በመተግበር ላይ ይገኛል። ይህ የማስፋፋት ምዕራፍ በ334 ወረዳዎች ውስጥ እየተተገበረ ሲሆን በማጠናቀቂያው ምዕራፍ ማለትም በ2019 ዓ.ም. 700 ወረዳዎችን የሚሸፍን ይሆናል። ሶስተኛው የማስፋት ምዕራፍ (Scale Up Phase) የሚባለውና ከ2019 - 2022 ዓ.ም በሀገሪቱ በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎች ውስጥ የሚተገበር ይሆናል።

ከኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት እና IFPRI (International Food Policy Research Institute) ጋር በትብብር በተደረገ የተጽዕኖ ግምገማ ጥናት መሰረት ባለፉት ሁለት አመታት በማስፋፋት ምእራፍ ውስጥ በተከናወኑ የብዝሐ ሴክተር ተግባራት በ2014 ዓ.ም ብቻ 59,711 ልጆችን ከመቀንጨር መታደግ የተቻለ ሲሆን በ2015 ዓ.ም ደግሞ 99,080 ልጆችን ከመቀንጨር መታደግ ተችሏል፡፡ የመቀንጨር ምጣኔው በዓመት ከ0.37 በመቶ (ጋምቤላ) እስከ 3.4 በመቶ (አማራ) ደርሷል፡፡

የሰቆጣ ቃልኪዳን እየስመዘገበ ያለው ውጤትን ከግምት በማስገባት መንግስት በያዓመቱ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ከትሬዠሪ በመመደብ በመደገፍ ላይ ሲሆን የክልል መንግስታት ለዚሁ ስራ አቻ በጀት ሲመድቡ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ የልማት አጋሮችና ለጋሾችም ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

የመንግስት መዋጮ በየዓመቱ እያደገ የመጣ ሲሆን በ2009 በ15 ሚሊዮን የተጀመረው የመንግስት ድጋፍ በ2016 750 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን የሚመጥን የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ባለመዘርጋቱ የተነሳ የተለያዩ ችግሮች ሲከሰቱ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ የነበረውን አሰራር ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

1. ቀደም ሲል መንግስት ለፕሮግራሙ የሚመድበውን በጀት የጤና ሚኒስቴር በባለቤትነት ተረክቦ ለክልል ፈጻሚ ሴክተሮች በማስተላለፍ ሲተገበር የቆየ ቢሆንም ይህ አሰራር የህግ ማዕቀፍ የሌለው መሆኑ፤
2. በዚሁ አሰራር መሰረት ጥቅም ላይ የዋለን ገንዘብ ለማወራረድ ሰነድ ከወረዳዎች ጀምሮ ወደ ጤና ሚኒስቴር ማመላለስ ማስፈለጉ፣ በዚህም የተነሳ ከፍተኛ የሰነድ ክምችት መፈጠሩና በጤና ሚኒስቴር ላይ ከፍተኛ የሆነ ተሰብሳቢ ገንዘብ መታየቱ፤በክልሎች የፋይናንስ መመሪያ የሚተገበሩ በመሆኑ ለኦዲት አስቸጋሪ መሆኑ፡፡
3. ቃልኪዳኑ በ15 ዓመት የሚተገበር ወረዳዎችም እየጨመሩ የሚሄዱ በመሆኑና በቀጣይ የሚኖረው የፋይናንስ አስተዳደር የመንግስትን የፋይናንስ ስርዓት ተከትሎ እንዲተገበር ማድረግ በማስፈለጉ፣
4. ለዚሁ ተግባር በክልሎች የሚመደብው አቻ በጀት የመንግስትን የፋይናንስ ስርዓት ተክትሎ ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ በማስፈልጉ ነው፡፡